የወ/መ/ቁጥር 165327

የልደታ ምድብ 1 ኛ ወንጀል ችሎ

ሐምሌ 12 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፡ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፡ 1 ኛ ወ/ሮ ፀሐይ አበበ አውራሪስ - ተወሰነ

2 ኛ አቶ ፍስሐፅዮን ተስፋማርያም - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

<u>ፍርድ</u>

ዐ/ሕግ የካቲት 05 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የወንጀል ክስ አቤቱታ ተከሳሾች በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1)(ሀ) እና 446(ለ) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ ተከሳሾች አቶ ጌታቸው ገ/ሚካኤል መሞታቸው እያወቁ በመዝገብ ቁጥር 135490 አንደኛ ተከሳሽ በከሳሽነት እና ሁለተኛ ተከሳሽ በአንደኛ ተከሳሽ ጠበቃነት በመሆን ታህሳስ 28 ቀን 2001 ዓ.ም መጥሪያ ሎሚች አቶ ጌታቸው ገ/ሚካኤል አስፈርሞ እንደሰጡ በማስመሰል የፈረሙበትን ማረጋገጫ በልደታ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 05/08 ክልል ውስጥ ለሚገኘው ለልደታ ምድብ 10 ኛ ፍ/ብሔር ችሎት ጥር 13 ቀን 2001 ዓ.ም ያቀረቡ በመሆናቸው በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈፀሙት የፍትህን ሥራ ማሳሳት ወንጀል ተከሰዋል በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሾች ደርሷቸውና ተነቦለቸው ከተረዱት በኋላ ለክሱ መቃወሚያ አቅርበው ውድቅ ከተደረገ በኋላ ድርጊቱን አልፈፀምንም፤ ጥፋተኞችም አይደለንም በማለት ክደው በመከራከራቸው ዐ/ሕግ ሦስት ምስክሮችንና የሰነድ ማስረጃዎችን አቅርቦ አስምቷል። የምስክሮቹ ቃልም ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል።

ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ከቀረቡት ማስረጃዎች ጋር በማገናዘብ የመረመረ ሲሆን በፍትሐብሔር መዝገብ ቁጥር 135490 ከሳሽ ወ/ሮ ፀሐይ አበበ በተከሳሽ አቶ ጌታቸው ገ/ሚካኤል ላይ ክስ አቅርበው ለተከሳሽ መጥሪያ እንዲያደርስ ጥር 12 ቀን 2001 ዓ.ም የተቀጠረ ሲሆን ይህ ለተከሳሽ ይድረስ የተባለው መጥሪያ ታህሳስ 28 ቀን 2001 ዓ.ም ወጪ የተደረገ ሲሆን በቀነ ቀጠሮው ማለትም ጥር 12 ቀን 2001 ዓ.ም ሬጅስትራር ፅ/ቤት በመቅረብ ተከሳሽ መጥሪያ አልቀበልም ብሏል በማለት ማረጋገጫ ያቀረበው ሁለተኛ ተከሳሽ ወይም በፍትሐብሔር መዝገቡ ጠበቃ የነበሩት አቶ ፍስሐፅዮን ተስፋማርያም ናቸው። ከዚያም በመቀጠል በችሎት ክሱ በተሰማ

ጊዜ ማለትም ጥር 13 ቀን 2001 ዓ.ም የቀረቡት አቶ ፍስሐፅዮን ተስፋማርያም እንጅ ወ/ሮ ፀሐይ አበበ አይደሉም። መጥሪያ ወጪ የተደረገው ታህሳስ 28 ቀን 2001 ዓ.ም በክሱ ተከሳሽ የነበሩት አቶ ጌታቸው ገ/ሚካኤል ግን ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ታህሳስ 21 ቀን 2001 ዓ.ም ስለመሆኑ የቀረበው የሐኪም/የሆስፒታል/ ማስረጃ ያረጋግጣል። ይህ ሆኖ እያለ አቶ ጌታቸው ገ/ሚካኤል በታህሳስ 28 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ መጥሪያ ቀርቦለቸው አልቀበልም ብለዋል ብሎ ለፍ/ቤት ማረጋገጫ በማቅረብ ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ በፍ/ቤት ታዞ እንዲወሰን መደረጉ የፍትህ ሥራን ማሳሳት በመሆኑ፤ ይህንንም የፈፀሙት ሁለተኛ ተከሳሽ በመሆናቸው፤ ሁለተኛ ተከሳሽ በተከሰሱበት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 446(ለ) ስር እንዲከላከሉ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(1) መሰረት እንዲከላከሉ ታዘዋል። አንደኛ ተከሳሽን በተመለከተ ግን መጥሪያውን ወጪ ስለማድረጋቸው ወይም በሁለቱም የፍ/ቤቱ ቀጠሮዎ ቀርበው ማረጋገጫ ያልሰጡ(ያላረጋገጡ) በመሆኑ እና በሌላ ሁኔታም የድርጊቱ ተካፋይነታቸው ያልተረጋገጠ ስለሆነ የወንጀል ሕግ አንቀፅ 446(ለ) ተጠቅሶ ከቀረበባቸው የወንጀል ክስ መከላከል ሳያስፈልጋቸው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 141 መሰረት በነፃ ተሰናብተዋል።

ሁለተኛ ተከሳሽ እከላከላለሁ ብለው አንድ የመከላከያ ምስክር አቅርበው ያሰሙ ሲሆን በመከላከያ ጭብጥነትም ያስመዘገቡት እኔ ጠበቃ ነኝ፤ መጥሪያ የመስጠት ኃላፊነት ባይኖርብኝም መጥሪያ ወጪ አድርጌ ለደንበኛዬ ስነግራቸው እኔ አሞኛል መጥሪያ ማድረስ አልችልም አድራሻው ግን እንደዚህ ቦታ ነው በማለት አቅጣጫውን ነግረውኝ፤ ብትችል እራስህ አድርስ ባትችል በመልዕክተኛ በኩል ስጠው ስላሉኝ እና የጠቆሙኝ ቦታ ራቅ ያለ በመሆኑና ትራንስፖርት ስለማይገባበት በዘወትር የሚላላከኝ አቶ ሰሎሞን ፀጋዬን ካለበት ጠርቼ በተጠቆምኩበት ቦታ መሰረት የላኩት ሲሆን፤ ቦታውን ፈልጎ ቤቱን አንኳኩቶና የአቶ ጌታቸው ገ/ሚካኤል ቤት ነው ብሎ ሲጠይቅ አዎ ሲባል፤ ቤቱን የከፈተው ግለሰብ ለምን መጣህ በማለት ሲጠይቀው መጥሪያ ለመስጠት ነው ሲለው፤ ና አምጣው ብሎ ተቀብሎ የፈረሙለት ሲሆን ይህን ተቀብዬ ነው በችሎት ያረጋገጥኩት የሚለውን አስመዝግቦ በዚሁ መሰረትም የመከላከያ ምስክሩ ቀርቦ በደንቡ መሰረት እንደ አምነቱ መጋላ ፈፅሞ የመከሰረ ሲሆን ቃሉም ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ይገኛል። የሰነድ የመከላከያ ማስረጃዎችንም አቅርበዋል።

ፍ/ቤቱም ሁለተኛ ተከሳሽ ባቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበባቸውን ክስና ማስረጃ አስተባብለዋል ወይ የሚለውን ነጥብ የመረመረ ሲሆን የሁለተኛ ተከሳሽ የመከላከያ ምስክር ቀርቦ እንዳስረዳው ሁለተኛ ተከሳሽ የፍ/ቤት መጥሪያ ለአቶ ጌታቸው ገ/ሚካኤል አድርስልኝ በማለት መጥሪያውን የሰጡኝና የአቶ ጌታቸው ገ/ሚካኤልን ቤትም አቅጣጫ ነግረውኝ፤ በነገሩኝ መሰረት በቤቱ ደርሼ ያንኳኳሁ ሲሆን፤ በጊዜው አንድ ግለሰብ በሩን የከፈተልኝ ሲሆን፤ እኔም መጥሪያ ለመስጠት ነው ስል በሩን የከፈተልኝ ግለሰብ በመጥሪያው ላይ ፈርሞ ሰጥቶኝ፤

ይህንኑ ለሁለተኛ ተከሳሽ ሰጥቻለሁ በማለት ነው የመሰከሩት። ሁለተኛ ተከሳሽም ይህንኑ አቶ ጌታቸው ገ/ሚካኤል ፈርመውበታል የተባለውን ሰነድ ለፍ/ቤት በማቅረብ በፍትሐብሔር ተከሳሽ የነበሩት አቶ ጌታቸው ገ/ሚካኤል መልስ ለመስጠት አልፈለጉም ተብሎ በሌሉበት ፍ/ቤቱ ውሳኔ የሰጠው። ይሁን እንጅ ሁለተኛ ተከሳሽ ለወ/ሮ ፀሐይ አበበ ጥብቅና ሲቆሙ ለተከሳሽ መጥሪያ ይሰጥ በተባለ ጊዜ መጥሪያውን ራሳቸው ከሳሽ የሆኑት ወ/ሮ ፀሐይ አበበ እንዲያደርሱ ማድረግ እንደሚገባቸው የታመነ ነው። ከዚህ ባለፈ ደግሞ ጠበቃው መጥሪያውን ለተከሳሽ ለሆነው ሰው ለማድረስ ከፈለጉ ወይም በደንበኛቸው እንዲያደርሱ ከታዘዙ ወይም መጥሪያ ለተከሳሽ ለማድረስ በውላቸው ላይ ከተስማሙ መጥሪያ የሚደርስለትን ግለሰብ ትክክለና አድራሻ አውቀው መጥሪያው ለራሱ ተከሳሽ ነው ለተባለ ሰው የደረሰ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው። አሁን ግን ሁለተኛ ተከሳሽም ሆነ የሁለተኛ ተከሳሽ የመከላከያ ምስክር የሆነው እንዳስረዱት የአቶ ጌታቸው ገ/ሚካኤል ቤት በየት ክፍለ ከተማ፤ ቀበሌና የቤት ቁጥር ውስጥ እንደሆነ በግልፅ ሳያስረዱ ወ/ሮ ፀሐይ አበበ በነገሩኝ አድራሻ መሰረት መጥሪያ እንዲያደርስ ለሚረዳኝ ሰራተኛ ነግሬው ሄዷል በማለት ሁለተኛ ተከሳሽ ሲገልፁ፤ የመከላከያ ምስክሩ ደግሞ ሁለተኛ ተከሳሽ በነገሩኝ አድራሻ መሰረት ሰዎችን ጠይቁ በነገሩኝ መሰረት ቤቱን አንኳኩቼ መጥሪያውን አስፈርሜያለሁ በማለት ይግለፅ እንጅ የት እንደሆነ ለችሎቱ አልገለፀም፤ ትክክለኛ የአቶ ጌታቸው ገ/ሚካኤልን ቤት አንኳኩቶ መጥሪያውን ለቤተሰቡ አባል ስለማድረሱም በተጨማሪ ምስክር ለማረጋገጥ አልቻሉም። መጥሪያውን ተቀብሎ ፊረመ የተባለው ግለሰብን ማንነትንም የሚታወቅበት ሁኔታ የለም። በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች የፍ/ቤቱ መጥሪያ ትክክለኛ ተከሳሽ ለነበረው ለአቶ ጌታቸው ገ/ሚካኤል ለራሳቸው ወይም ለቤተሰብ አባላቸው የመከላከየ ምስክሩ ያደረሰ ስለመሆኑ አልተረጋገጠም። ይህ ደግሞ የሰራተኛው የአቶ ሰለሞን ፀጋዬ ጥፋት ነው። ይህን ሰራተኛ ደግሞ የተወሰነ ክፍያ እየከፈለ የሚያስራው ሁለተኛ ተከሳሽ ስለሆነ በፌደራል ፍ/ቤቶች ጠበቆች የሥነ ምግባር ደንብ ጥር 57/1992 አንቀፅ 40(2)(ሀ) መሰረት ተጠያቂ የሚያደርጋቸው ድርጊት ነው። ሁለተኛ ተከሳሽ የተወሰነ ክፍያ እየከፈሉ የሚያስሩት አቶ ሰለሞን ፀጋዬ መጥሪያ ለትክክለኛው ተከሳሽ አቶ ጌታቸው ገ/ሚካኤል ማድረሱን ሳያረጋግጡ ፍ/ቤት ቀርበው መጥሪያው ለተከሳሹ ደርሶታል በማለት ማረጋገጫ የሰጡና በዚሁ ምክንያት ፍ/ቤቱ ተከሳሹ መጥሪያ እንደደረሰው በመቁጠር ተከሳሹ በሌሉበት ውሳኔ እንዲሰጥ በማድረጋቸው፤ ይህ ድርጊት ደግሞ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 446(ለ) መሰረት ክልከላ የተደረገበት ስለሆነ፤ ሁለተኛ ተከሳሽ ባቀረቡትም የመከላከያ ማስረጃ ይህንኑ የወንጀል ደርጊት ለማስተባበል ያልቻሉ ስለሆነ በዚሁ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 446(ለ) ስር ጥፋተኛ ናቸው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>የቅጣት አስተያየት</u>

<u>ዐ/ሕግ</u>፡ የቅጣት ማቅለያ የለንም፤ ነገር ግን የቅጣት ማክበጃ በማለት በወንጀል

ሕግ አንቀፅ 84(1) (ለ) መሰረት ተከሳሹ የተጣለበትንና የተሰጣቸውን እምነት ወደ ጎን ትተው ድርጊቱን የፈፀሙ ስለሆነ እንዲሁም በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84(1) (ሠ) ደግም ድርጊቱ የተፈፀመ በፍ/ቤት ላይ ስለሆነ ቅጣቱ ከብዶ እንዲወሰን በማለት አመለከተ።

<u>ተከሳሽ</u>፡ ዕድሜዬ 63 ዓመት ነው፤ የትምህርት ደረጃዬ የዩኒቨርሲቲ ድኘሎማ ነው፤ ልጆች ሰባት ያሉኝ ሲሆን አምስቱ አስራ ስምንት ዓመት ያልሞላቸው ናቸው፤ ባለቤቴ የቤት እመቤት ናቸው፤ ሥራ የላቸውም፤ የወር ገቢዬ ከጡረታ ጋር ብር 1000.00(አንድ ሺህ ብር) ነው፤ እናትና አባቴ ደካሞች ናቸው፤ እኔም ደካማ ነኝ፤ በሰው ሰራሽ እግር ነው የምንቀሳቀሰው፤ ድርጊቱም የተፈፀመው እኛ በተለመደው የጠበቆች አስራር መሰረት ስለሆነ ፍ/ቤቱ ይህንኑ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ቅጣቱን እንዲወስንልኝ በማለት አመለከቱ።

ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ቅጣት ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ሊሆን እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወስነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ክብደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ

የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

ተከሳሹ አሁን ጥፋተኛ የተባሉበት በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 446(ለ) /የፍትህን ሥራ ማሳሳት ወንጀል ገና ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ የወንጀል ደረጃ እና እርከን የሚወሰነው በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 13 መሰረት ነው። የደረጃ አወሳሰኑም ማክበጃውና ማቅለያው ታሳቢ ከመደረጉ በፊት በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት እንደሚወሰን መመሪያው በደነገገው መሰረት ደረጃው በሦስት ደረጃዎች ሀ. ዝቅተኛ፤ ለ. መካከለኛ እና ሐ. ከባድ ደረጃ በማለት ይለያል።

ፍ/ቤቱም በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት ወንጀሉ የተፈፀመው ሁለተኛ ተከሳሽ በተለመደው የጥበቅና ሙያ አሰራር መጥሪያውን ለሚላላካቸው ግለሰብ በመስጠት የተፈፀመ እና ግለሰቡንም ለመርዳት ጭምር ስለሆነ ከባድ የማይባል ቢሆንም ከሙያቸው አንፃር ግን ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊያደርጉበት የሚገባ ስለሆነ ድርጊቱ ቀላል ባለመሆኑ የወንጀል ደረጃው መካከለኛ ነው ተብሎ ተወስኗል።

በወጣው ደረጃ መሰረት ቅጣቱን ለመወሰን በሕጉ አንቀፅ 446(ለ) ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ በመቀጮ ያስቀጣል ተብሎ የተደነገገ ስለሆነ ከሁለቱ የቅጣት አይነቶች ፍ/ቤቱ በቅድሚያ አንዱን መምረጥ ስላለበት ከተከሳሽ እድሜ ከፍተኛነት አንፃር እና ሰባት ልጆችን የሚያስተዳድሩ ከመሆኑ አንፃር በእስራት ከመቅጣት በገንዘብ መቀጮ መቅጣት አግባብ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ተከሳሽ በገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ወስኗል።

ፍ/ቤቱ ተከሳሽን በገንዘብ መቀጮ እንዲቀጡ ከወሰነ ደግሞ በመመሪያው አንቀፅ 13(10) መሰረት የሚወሰን ሲሆን፤ በዚህም መሰረት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 446(ለ) የገንዘብ መቀጮው ከብር አስር እስከ አንድ ሺህ ብር ስለሆነና የወንጀል ደረጃው መካከለኛ በመሆኑ መነሻ ቅጣቱ ከጣሪያው ብር አንድ ሺህ በአንድ ሦስተኛ ዝቅ ብሎ ተሰልቶ ከሚገኘው ውጤት ጣሪያ ሳይበልጥ ይወሰናል። የብር አንድ ሺህ አንድ ሦስተኛ ውጤት ብር ሦስት መቶ ሰላሳ ሦስት ብር ስለሚሆን ቅጣቱ በብር ሦስት መቶ ሰላሳ ሦስት እና በዚህ አሁን በስሌቱ መሰረት በተገኘው ውጤት ብር ስድስት መቶ ስልሳ ሰባት ብር መካከል ይወሰናል። ፍ/ቤቱም የተከሳሽ የወር ገቢን መሰረት በማድረግና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆናቸውን ከግንዛቤ በማስገባት ቅጣቱ ብር 600.00(ስድስት መቶ ብር) መነሻ ቅጣት እንዲሆን ተወስኗል። ይህን መነሻ ቅጣት ይዘን ወደ መመሪያው አባሪ ሁለት ስንሄድ ይህ የብር 600.00(ስድስት መቶ ብር) የገንዘብ መቀጮ በአባሪ 2 እርከን 1 ስር የሚወድቅ በመሆኑ፤ የእርከን 1 ፈቃደ ስልጣን ደግሞ እስከ ብር አንድ ሺህ ድረስ ስለሆነ ፍ/ቤቱ በዚሁ ፍቅድ ስልጣን መሰረት ሁለተኛ ተከሳሽ በብር 800.00(ስምንት መቶ ብር) እንዲቀጡ ተወስኗል።

በዐ/ሕግ በኩል የቅጣት ማክበጃ የቀረበ ቢሆንም ሁለተኛ ተከሳሽ የተጣለባቸውን እምነት አለአግባብ ተገልግለዋል ለማለት በጥብቅና ውላቸው ወይም በሕግ መጥሪያ ራሳቸው ማድረስ አለባቸው የሚል የተለየ እምነት የተጣለባቸው መሆኑን ዐ/ሕግ ያላስረዳ ስለሆነ እንዲሁም የወንጀል ሕግ አንቀፅ 84(1)(ሠ) ተጠቅሶ የቀረበውን በተመለከተም ሁለተኛ ተከሳሽ በፍ/ቤቱ ውስጥ ባለ አንድ ችሎት ውስጥ ይህንን ድርጊት መፈፀማቸው በሕግ በተቋቋመ ባለስልጣን ላይ ድርጊቱን ፈፅመዋል የማያስብል ስለሆነ ፍ/ቤቱ የቅጣት ማክበጃ ምክንያቱን አልተቀበላቸውም። በመሆኑም ከላይ የተወሰነው ቅጣት የሚከብድበት ምክንያት የለም። በተከሳሽም በኩል በማስረጃ የተደገፈ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ስላልቀረበ ፍ/ቤቱ ከላይ የወሰነውን መጠን ብር 800.00(ስምንት መቶ ብር) ን ተከሳሽ በመቀጮነት እንዲከፍሉ ወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. ተከሳሽ ቀደም ሲል ለዋስትና ያስያዙት ገንዘብ ለቅጣቱ ዓላማ ይዋል።

2 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

3 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።